# አብዮታዊት ኢትዮጵያ

23



መጋቢት ፴ — ፲፱፻፸፱ ዓ.ም.

## ርእሰ አንቀጽ

# የአዞ ዕንባ

በመደብ በተከፋፈሉ ኅብረተሰቦች ውስጥ ለበዝባዥና ለተበዝባዥ መደቦች አንድ ዓይነት ትርጉም ያላቸው ብዙ ነገሮች የሉም ፤ ለበዝባዥ መደብ ጥሩ የሆነው ነገር ለተበዝባዥ መደብ ደግሞ መጥፎ ነው ። የበዝባዦች ፍትሕ አለ ፤ የተበዝባዦችም ፍትሕ አለ ፤ የበዝባዦች ነፃነት አለ ፤ የተበዝባዦችም ነፃነት አለ ፤ የበዝባዦች ዲሞክራሲ አለ ፤ የተበዝባዦችም ዲሞክራሲ አለ ።

በዝባዦቹ ነፃነት የሚሉት ሰፊውን ሕዝብ እንደልብ ለመዝረፍ ለመበዝበዝና ለመጨቆን ያላቸውን ነፃነት ነው ። ሰፊው ሕዝብ ደግሞ ነፃነት የሚለው ከጥቂቶች ጭቆናና ብዝበዛ ተላቅቆ ለመኖር ያለውን ነፃነት ነው ። በዝባዦች ዲሞክራሲ ሲሉ ለነርሱ መደብ የሚያመች ዲሞክራሲና በተበዝባዥ መደቦች ላይ የሚጭኑትን የባርነት ቀንበር ነው ። ሰፊው ሕዝብ ደግሞ ዲሞክራሲ ሲል ለሰፊው ሕዝብ ወገኖች ነፃነትንና በበዝባዥ መደቦች ላይ አምባገነንነትን ማመልከቱ ነው ።

የሰብአዊ መብቶች ጉዳይ መታየት ያለበት ከመደብ አንፃር እንደሆነ ግልጽ ነው ። ተንኮታኩቶ በመውደቅ ላይ ያለው የፊውዶ ፋሽስቱ ሥርዓት በሀገራችን ላይ ተንሠራፍቶ በቆየበት ዘመን ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ ምንም ዓይነት መብቶች አይታወቁለትም ነበር ። እንዲያውም ሰብአዊ መብቶች ተረግጠው የሶሻልና የኤኮኖሚ ፍትሕ ተነፍጎ ፤ በፊውዳል ጭቆና ሲማቅቅ ብዙ ዘመናት አሳልፏል ።

በተለይም የፊውዶ ካፒታሊስቱ ሥርዓት መስፋፋት ከጀመረ ወዲህ ፤ የፋሽስቱን የኃይለ ሥላሴን እሥር ቤቶች የሚያጫንቁት ጭቁኖች ነበሩ ። መሬት ላራሹ ይሁን የሚለውን ሥርነቀል ጥያቄ አንስተው የታገሉት ወጣቶች በየአደባባዩ ተጨፍጭፈዋል ፤ በየወህኒ ቤቱ ተሰቃይተዋል ። ድኃ ገበሬዎች የወዛቸውን ፍሬ በመሬት ከበርቴዎች ከመነጠቃቸውም በላይ ይህን ታክስ ካልከፈላችሁ ይኸኛውን ግብር ካላሟላችሁ እየተባሉ በበረት እንደሚታጎር ከብት በየእስር ቤቱ እየታጨቁ ተንገላትተዋል ። ጭቁን ወዝ አደሮችም ብዝበዛን ለመቃወም ድምፃቸውን በማሰማታቸው ከሥራ ተባርረዋል ፤ በየእሥር ቤቱ ተግዘው ፍዳ አይተዋል ። ተራማጅ ዜጎችና ሀገር ወዳዶች ሁሉ ፊውዶ ፋሽስቱን ሥርዓት በመቃወማቸውና በድፍረት በማጋለጣቸው በእሥር ቤት ተጨብጠዋል ። ወደ እየበረሃው ተግዘው አእምሮዋቸውን እንዲስቱ ተደርገዋል ። እንግዲህ ይህ በግልጥ የሚያሳየው ባለፈው ሥርዓት የሚታሰሩት ፤ የሚገደሉትና የሚጉላሉት ፤ የጭቁን መደቦች አባሎች እንደነበሩ ነው ። ጊዜው ጭቁኖች ሰብአዊ መብታቸውን ተገፍፈው በጭካኔ የተጣሉበት ነበር ።

አብዮቱ በመጋጋል ላይ ባለበት ባሁኑ ወቅት ደግሞ ሁኔታው ተቀይሯል ። ጊዜው ሰፊው ሕዝብ መብቱንና ጥቅሙን በትግሉ የሚያስከብርበት ነው ። ስለዚህም « መሬት ላራሹ » ከመፈክርነት ወደ ገቢር መለወጡን የሚቃወሙ ፤ የማምረቻ መሣሪያዎች ወደ ሕዝብ መዛወሩን . . . ወዘተ የሚፃረሩ በቁጥጥር ላይ የሚውሉበት ጊዜ ነው ። ባጠቃላይ ብዝበዛ ካልቀጠለ ብለው የሚሟገቱ በሕዝቡ ክንድ የሚደቆሱበት ሰዓት ነው ። ያለፈውን የወደቀ የምዝበራ ሥርዓት ለማስነሳት የሚታገሉ የሚመነጠሩበት ፤ የተወናበዱም የሚታረሙበት አብዮታዊ ወቅት ነው ። ስለሆነም ፀረ— ሕዝብ ወገኖች ጨለማ ይዋጣቸው እንጂ ፤ የሰፊው ሕዝብ ወገኖች ፤ ከመቼውም ይልቅ ዛሬ መብታቸው መሟላት የጀመረበት የትግል አፍላ ነው ።

ሐቁ ይህ ሁኖ ሳለ አድኃሪ ኃይሎች ግን ሁኔታውን የሚመለከቱት የተገላቢጦሽ ነው ። የትናንትናው የኃይለ ሥላሴ ፋሽስታዊ አገዛዝ ለነርሱ የነፃነትና የመብት ዘመን ነበር ። ለምሳሌ እነ ኢ.ሕ.አ.ፓ. « ዛሬ ነፃነት ጠፋ» ብለው በማማረር የሚጮሁት ለዚህ ነው ። «አምነስቲ ኢንተርናሽናል » ለተባለው ድርጅት ባስተላለፈው መልእክት አድኃሪው ኢ.ሕ.አ.ፓ «ባለፉት ሁለት ዓመታት የኢትዮጵያውያን መብቶች ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ተደፍረው ነበር » ብሎ የኢትዮጵያን አብዮት ለማጥላላት የሞከረውም በዚሁ ምክንያት ነው ።

ካንዱ አድኃሪ ወደ ሌላው ይህ ክስ አሁንም በቅብብሎሽ መተላለፉ አልቆመም ። ይኸው አምነስቲ ኢንተርናሽናል ባለፈው ሰሞን የኢትዮጵያን አብዮት ለአሜሪካን ኮንግሬስ ሲከስስ « ኢትዮጵያ ውስጥ ሰብአዊ መብቶች ተገፍፈዋል » ሲል ጽፏል ። ይህ ድርጅት በትክክል ግልባጭ የሚያስተጋባው ልክ የአድኃሪዎችን የኢዲዩንና የኢ.ሕ.አ.ፓን ጩኸት ነው ። ኢ.ሕ.አ.ፓም ይህንኑ ፀረ—ሕዝብ ክሱን ሲደረድር ፤ «በኢትዮጵያ ውስጥ ይህ ሁሉ የሚፈጸመው ዓለም አቀፍ ተቃውሞ ባለመኖሩ ነው » በማለት ፤ ዓለም አቀፍ አድኃሪ ኃይሎች በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ እንዲገቡ ጋብዟል ። ከዚሁ አድኃሪ ጋር አቋሙን ባንድነት ያሠለፈው « አምነስቲ ኢንተርናሽናልም » ይህንኑ ጩኸት በቀጥታ በማስተላለፍ የአሜሪካን መንግሥት በኢትዮጵያ ጉዳይ ጣልቃ ገብቶ አብዮቱን እንዲያደናቅፍ ጥሪ አድርጓል ።

የነአምነስቲ ኢንተርናሽናል ፀረ—አብዮት ፕሮፓጋንዳ ዓለም አቀፍ ኢምፔሪያሊዝም በአብዮቱ ላይ ከሚያደርገው የቅልበሳ ዘመቻ ተነጥሎ የሚታይ አይደለም ። የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ትክክለኛውን የአብዮት ሂደት እንዳይረዱ ድሉን ጥላት ቀብቶ ያቀርባል ። ሙከራው ሁሉ ባይሳካለትም ፤ አብዮቱን ብቸኛ አድርጎ ወዳጅ ለማሳጣት ይጥራል ። አብዮቱን አጥላልቶና አጣምሞ በማቅረብም አብዮታዊ ትግል መካሄዱን ለማስካድ በብርቱ ይታገላል ።

በጣም የሚገርመው ግን ፤ ትናንት የኢትዮጵያ ሕዝብ በረኃብና በቸነፈር ሲረግፍ ቃል ያልተነፈሰው አምነስቲ ኢንተርናሽናል ዛሬ መብት አስከባሪ ሆኖ መቅረቡ ነው ። ለመሆኑ የኢትዮጵያ ጭቁኖች በነኃይለ ሥላሴ ጅራፍ ጀርባቸው ሲላጥ አምነስቲ የት ነበር ። የኢትዮጵያ ተራማጆች በፋሽስቱ ፊውዳል መንግሥት ወህኒዎች ቅሰማቸው ሲሰበርስ አምነስቲ ወዴት ተሠውሮ ነበር ። ዛሬ የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ የምርቱና የመብቱ ባለቤት እየሆነ ሲሄድ « በኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ጠፉ» እያለ ሲያላዝን ለኢትዮጵያ ጭቁኖች ማፍሰስ የጀመረው ዕንባ የአዞ ዕንባ እንደሆነ መታወቅ አለበት ።

ከዚህም አልፎ ይህ ጩኸቱ የዓለም አድኃሪ ኃይሎች ከኢ.ሕ.አ.ፓ. ፤ ከኢ.ዲ.ዩ. ፤ ከኢ.ኤል. ኤፍ. ጋር ተባብረው የቀድሞውን ሥርዓት በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ መልሶ ለመጫን የሚያደርጉት ጥሪ እንደሆነ ይገባናል ። ይህንን ግን ፈጽሞ ለማድረግ እንደማይችሉ እናውቃለን ። ለነፃነቱ ለመብቱና ለሰብአዊ ክብሩ ለመታገልና ለመሞት ከዳር እስከ ዳር የተነሳሳው ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ በነቃ በተደራጀና በታጠቀ አመፅ ጠላቶቹን ሁሉ ደምስሶ አብዮቱን ከግቡ ያደርሳል ።

አብዮታዊት ኢትዮጵያ
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው ።